# የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ
# ድጋፍ ኮሚቴ - ቦስተን

**955 Mass. Ave. P.O.Box 341**
**Cambridge, MA 02139**
**E-mail: cudboston@yahoo.com**


**ቁጥር፡** 07/001/2006
**Ref. Nº**
**ቀን፡** July 15, 2006

## በማሳቹሴትስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ኅብረት ያቀረበው ቅሬታና ከጀርባው ያለው እውነታ ለመግለጽ ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የቦስተን ድጋፍ ኮሚቴ የተሰጠ የጽሑፍ መግለጫ

አቡጊዳ የኢትዮጵያን አሜሪካን ቴሌቪዥን ኔትወርክ የማሳቹሴትስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ኅብረት June 18, 2006 ተዘጋጅቶ የነበረውን የውይይት መድረክ አስመልክቶ ባቀረበው ሪፖርት ላይ የተሰማውን ቅሬታ በኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ ሬዲዮ ባለፈው July 9, 2006 ማሰማቱ ይታወሳል፡፡ ይህንንም ቅሬታ የቦስተንና አካባቢው የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በጥሞና ተከታትሎታል፡፡ በተዘጋጀው ውይይት ላይ ቅንጅት እንዲሳተፍ ጥያቄ ቀርቦ እንደነበርና እንዲሁም ከጀርባ ያለውን ታሪክ አያይዞ ማቅረብ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የተማሪዎች ማኅበር ያሰማውን ቅሬታ ስንመለከተው የቅሬታው ዓብይ ነጥብ አቡጊዳ ማኅበሩ ስላደረገው ውይይት ያቀረበው ሪፖርት በአሉባልታ፣ በሀሜትና በውሸት ላይ የተመረኮዘ ውንጀላ ነው ብሎታል፡፡ በዚህም ማኅበሩ በጥልቅ ማዘኑን አስገንዝበዋል፡፡

በቀረቡት የቅሬታ ነጥቦች ግን ውሸቱ፣ አሉባልታውና ሀሜቱ የትኛው እንደሆነ የተገለጸ የለም፡፡ ማኅበሩ በጉዳዩ በጥልቅ ማዘኑን ቢገልጽም ምክንያቶቹን አልዘረዘረም፡፡ ቅሬታው እንዲያው «ሾላ በድፍን» ነው፡፡ አንድ አባባል በማስረጃ ካልተደገፈ እራሱ ተመልሶ በሌላው ወገን ላይ ስድብና ዘለፋም ይሆናል፡፡ ይልቁንም ሊያዝኑ የሚገባቸው የአቡጊዳ ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢ የሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡ እነኚህ ወጣቶች የስብሰባውን ጥሪ ማስታወቂያ ሰምተው፣ አጀንዳውን ተረድተው፣ የሚደረገውን ውይይት አድምጠው ሂደቱን በፊልም ቀርጸው ከምሁራን የሚፈልቀውን ቁም-ነገር ለሕዝብ አቀነባብረው ለማቅረብ ዝግጁ ሆነው ሲጠብቁ የአደባባዩ ጥሪ እንደግለሰብ ስብሰባ ተቆጥሮ ሂደቱን በፊልም መቅረጽ አትችሉም ተብለው የተከለከሉት፡፡ እነዚህ ወጣቶች ያለአንዳች ክፍያ ለወገን አገልግሎት ለመስጠት ደፋ - ቀና የሚሉ ናቸው፡፡

ማኅበሩ በአቡጊዳ የቀረበውን ሪፖርት እንደ «መናቆር» ም ተመልክቶት ስጋት አድሮበታል፡፡ በእኛ በኩል ይህ በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ እሰጥ አገባ እንደ «መናቆር» አልተመለከትነውም፡፡ የንግግር ነፃነታችንን ለማዳበር በአግባቡ ከተጠቀምንበት በሂደቱም አንዱ ሌላውን ከጥፋትና ከስህተት የሚቆጥብና የሚያስተምርበት መድረክ ነው፡፡ ከልዩነት ነጥሮ የሚወጣውም ቁም-ነገር ጥሎት የሚያልፈው ትምህርት ሁሉንም ወገን ከዳግም ስህተት ይጠ ብቃል፡፡ የሚዲያም ሥነ-ምግባር (Media Ethics) መሠረታዊ አሰራር አስተሳሰብም ይሄው ነው፡፡

955 Mass. Ave. P.O.Box 341
Cambridge, MA 02139
E-mail: cudboston@yahoo.com


---

በእኛ እምነት የቀረበው ጽሑፍ ከጀርባው ለብዙዎች ግልጽ ያልሆነ ታሪክ አለው። ብዙኃኑ የተማሪዎች ማኅበር አመራር አካላት ታሪኩን የተረዱና የስትራቴጂውንም ምስጢር የተካፈሉ አይመስለንም። በአመራሩ ዙሪያ የጉዳዩ ንቁ ተሳታፊና አንቀሳቃሽ የሆኑት አጀንዳው ምን ላይ እንዳነጣጠረ በውል ተረድተው ቅንጅት በውይይቱ እንዲሳተፍ ጥያቄውን ሲያቀርቡ ጉዳዩ ወቅታዊ ያለመሆኑንና ባቀራረቡና በይዘቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወቅታዊና አንገብጋቢ የፖለቲካ ዲሞክራሲ ጥያቄ የሚያዘናጋና የሚያረሳሳ፤ ለውጪውም ዓለም በጠመንጃ አፈ-ሙዝ ስር ያለውን ሕዝብ ሰላም ያለው ለማስመሰል የታቀደ ወያኔ የተንኮል ሴራ መሆኑን አስረድተናል።

በእኛ በኩል አሁንም የዚህ አጀንዳ ባለቤት ወያኔና ጀሌዎቹ እንደሆኑ ማረጋገጥ እንወዳለን። ዛሬ ገዢው ፓርቲ በሙያ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በፖለቲካ መሪነት በድምጽ አንጥሮ ያወጣቸውን ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች በቃሊቲ እስር ቤት አጉሮ በሀገር መክዳትና በዘር ማጥፋት የፈጠራ የወንጀል ክስ አቅርቦባቸው ለሰይፍ እያዘጋጃቸው ይገኛል። ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት አቤቱታ ለማሰማት አደባባይ የወጡትን የኢትዮጵያ ወጣቶችን በጠራራ ፀሐይ ያለምህረት ለጥይት አረር ዳርጓቸዋል። ከእነዚህ መካከል የነፃው ፕሬስ አባላት ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ ሆነው ይገኙበታል። ግፉ ዛሬም እንደቀጠለ ነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዛሬም ለግፉ አልተንበረከኩም። የትግል ስልታቸውን እየለዋወጡ የግፍ አገዛዙን በመታገል ላይ ይገኛሉ። የድረሱልን ጥሪያቸውም ያስተጋባል። በአሜሪካን ግዛቶች በየቦታው የተደራጁትም የኢትዮጵያ ተማሪዎች የድጋፍ አጋርነታቸውን በልዩ ልዩ መልክ በማሳየት ላይ ይገኛሉ።

በማሳቹሴትስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ኅብረት ለሀገራቸውና ለወገናቸው ችግር መርጃ ያደረጉትን እንቅስቃሴዎች ለማኮሰስ አይዳዳንም። ለረሀብ ዕርዳታ በማስተባበር ገንዘብ አሰባስበዋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ባህልና ወግ፤ ታሪኩንና ማንነቱን፤ የረሀቡንም ችግር በማሳወቅ በጎ አስተዋጽዎ አስመዝግበዋል። የዛሬው የሀገሪቱ ችግር ደግሞ ጠንከር ያለ ጥረት ይጠይቃል። ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ የገጠመው ታላቅ የፖለቲካ ቀውስና ምስቅልቅል የወያኔ የተዛባ ሥርዓት የፈጠረው ችግር ነው። ይህ ችግር የሚፈታው የመንግስትን ኃይል ይዞ የሚገኘው ወያኔ በእሥር ላይ ከሚገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎች ጋር በመነጋገር ብቻ ነው። ዛሬ የዓለም ዓቀፍ ተጽዕኖም በወያኔ ላያ እየበረታ ያለው በዚህ አቅጣጫ ነው። መለስ ከእዚህ ተጽዕኖ ለማምለጥ በሕዝቡ ላይ የአፈና ክንዱን እያጠናከረ ይገኛል። ይሁንና ዓለም ተንኮሉን በውል ስለተረዳው በሥርዓቱ ላይ ቁልፋና መሠረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀምሯል። ብዙዎቹም በአደባባይ ወጥተው የሥርዓቱን ማንነት በማጋለጥ ላይ ይገኛሉ። የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች፤ የሕግ ማመንጫ ተቋማት፤ የፕሪስ ነፃነት ተከራካሪ ኃይሎች፤ ልዩ ልዩ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና መንግስታት በልዩ ልዩ መልክ የተጽዕኖ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛሉ። ይህ አካሄድ ያስደነገጠው ገዢ ፓርቲ አርፎ አልተቀመጠም። የውጭውን ዓለም ተጽዕኖ በማስገኘት ዓብይ ሚና

# የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድጋፍ ኮሚቴ - ቦስተን

955 Mass. Ave. P.O.Box 341
Cambridge, MA 02139
E-mail: cudboston@yahoo.com


ከተጫወቱት መካከል በልዩ ልዩ ሀገሮች በዲያስፖራ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስለመሆናቸው ያካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎች፤ የረሀብ ዐድማዎች፤ ያወጡዋቸው ጽሑፎችና ሕዝባዊ ስብሰባዎች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ገዢው ፓርቲ ይህን ስለተገነዘበ የነደፈው ባለ 52 ገጽ የስትራቴጂ ዕቅድ የዚህ ጥያቄ ምላሽ ነው። በዚህ ስትራቴጂ መሠረት የወያኔ ኢህአዴግ ካድሬዎች በየውጭ ሀገሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንን በጥቅማ ጥቅም አጥምዶ ድምጽ ለሌለውና ለታፈነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ሆነው እየጮሁለት ያሉትን ልጆቹን ከትግሉ ለማዘናጋትና የወያኔ ኢህአዴግ አስተዳደር የተረጋጋ ነው ለማሰኘት በስልት እያደባ በየቦታው ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ጀምሯል። የወቅቱ ዋነኛውም ስልት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የውይይት ፎረሞች በማዘጋጀት የኢትዮጵያን ዓብይ አነጋጋሪ ጉዳይ ለማስረሳት ያልተዛመዱ አጀንዳዎችን ለሕዝብ ውይይት በማቅረብ አቅጣጫ ማስለወጥ ነው።

በአካባቢያችንም June 18, 2006 በተማሪዎች ማኅበር አመራር የተጠራ የውይይት መድረክ ስብሰባ የዚሁ ሴራ አካል ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ብዙኋን የተማሪው ማኅበር አመራር አባላት ይህንን ሴራ የተገነዘቡት አይመስለንም። የሴራው ሚስጥር ተካፋይ ግን ከውስጣቸው እንዳሉ ግን አጠያያቂ አይደለም። ለእነሱ ያለን መልዕክት ግልጽ ነው። ሰው የሚያምንበትን አትከተል አይባልም። በእምነት የመጓዝ ነፃነት ለእያንዳንድችን ሊከበርልን ይገባል። የተመረጡበትን ሀላፊነት የግል እምነት መጠቀሚያ ማድረግ ግን በሕግም በሞራልም የሚደገፍ አይደለም። የተማሪ ማኅበር በኢትዮጵያ በፍትህና በነፃነት ጥያቄ ላይ ብዙ ታሪክ ያስመዘገበ ኃይል ነው። የተማሪው ማኅበር በእነዚህ ጭብጦች ዙሪያ ብቻ ይወሰን ማለታችንም አይደለም። የሙያና የአካዳሚ ዕድገትን ለማዳበር የሚካሄዱ ውጥኖች መኖር ይገባቸዋል። መበረታታትም አለበት። በዚህ ጉዳይ ያሳዘነንና ህሊናችንን በጥልቅ የቆረቆረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በድምጹ የመረጣቸውን መሪዎች ዘብ ጥያ ተወርውረው የሰመዓታት ደም ሳይደርቅ፤ የሰቆቃ ድምጻቸው ከአይምሯችን ሳይፋቅ፤ አንድም ለዘላለም ባርነት አሌያም ለዘላቂ ነፃነት የሚደረገው ትግል በፍልሚያ ላይ እያለ ዓብዩ የሀገር አጀንዳ እንዴት ገሸሽ ለማድረግ ተሞከረ የሚሆን ይሆናል።

ዛሬም ለተማሪው ማኅበር አመራር የምናስተላልፈው መልዕክት የዲሞክራሲን ሥርዓት በኢትዮጵያ ለማስፈን የሚደረገው ጥረት በጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች የተተወ ጉዳይ አይደለም። ትግሉ የዲሞክራሲና የሕግ ልዕልና የተረጋገጠበት ሥርዓት በመፍጠር ሁሉም በነፃነትና በኢትዮጵያዊነቱ በእኩልነት ኮርቶ እንዲኖር ዋስትና ማበጀት ስለሆነ የሁሉንም አስተዋጽዎ ይሻልና እየተራረምን ተቀራርበን እንድንሰራ ጥሪ እናቀርባለን።

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!!!**

**የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድጋፍ ድርጅት**
**ቦስተን**